Queensland Health

# የመድብለ ባህላዊ የጤና ፖሊሲና የድርጊት መርሃ ግብር 2024–2029 MHPAP

**በኩዊንስላንድ ውስጥ ያሉ ከመድብለ ባህላዊ ታሪክ/ዝርያ የመጡ ሁሉም ሰዎች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ባህላዊ ተገቢ የህዝብ ጤና አጠባበቅ ፍትሃዊ ውጤት ማግኘት ይችላሉ።**



Interpreter

## መርሆዎች

- **የጤና ፍትሃዊነት፣ ደህንነት እና ጥራት ያለው እንክብካቤ**
- **በማስረጃ ላይ የተመሰረተ እና በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ**
- **ሁለንተናዊ እንክብካቤ**
- **ዘረኝነትን እና አድልዎ መፍታት**
- **የጋራ ቁርጠኝነት፣ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት**





MHPAP ለሁሉም የመድብለ ባህላዊ ህዝቦች የጤና ውጤቶች ላይ ያተኩራል። የሚከተሉትን ሰዎች ጨምሮ፡-

- በአውስትራሊያ ውስጥ የተወለዱ ግን በባህር ማዶ የተወለዱ ወላጆች ወይም አያቶች ያሏቸው
- እንደ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች ሆነው ወደ አውስትራሊያ የተሰደዱ
- ጊዜያዊ ቪዛ ያላቸው የኒውዚላንድ ዜጎች
- ወቅታዊ ሰራተኞች፣ አለም አቀፍ ተማሪዎችና ሌሎች ወደ ጊዜያዊ ቪዛ የሚያመሩ መንገዶች ያሏቸውን ያካተተ፣ የተወሰነ የሜዲኬይር ኣገልግሎት ብቻ ያለበት ጊዜያዊ ቪዛ ያላቸው ሰዎች፣
- የአውስትራሊያ ደቡብ ባህር ደሴት ነዋሪዎች።

**MHPAP ምክክር**

725 ሰዎች

27 ድርጅቶች

ሁሉም ግዛቶች ያዳረሰ

**MECHANISMS**
22 የታለሙ ዎርክሾፖች
15 የቀረቡ ጽሑፎች
43 የአንድ ለአንድ ግንኙነቶች
161 የዳሰሳ ጥናት ምላሾች

MHPAP የመድብለ ባህላዊ ህዝቦችን ጤና ለማሻሻል ያለመ የኩዊንስላንድ ጤና ከ10 አመታት በላይ ያዘጋጀው የመጀመሪያው ፖሊሲ ነው።

የማህበረሰብ ድምጽ በጤና ስርአታችን ፖሊሲ ውስጥ መንጸባረቁን ለማረጋገጥ MHPAP፣ የማህበረሰቡ አባላትና ድርጅቶችን ጨምሮ፣ ከብዙ ባለድርሻ አካላት፣ ጋር በጋራ የተዘጋጀ ነው።

ለመድብለ ባህላዊ ማህበረሰቦች የጤና ፍላጎቶች የተሻለ ምላሽ እንድንሰጥ MHPAP በጤና ስርዓቱ ውስጥ ፕሮግራሞችንና ተነሳሽነቶችን ያቀርባል። የኩዊንስላንድ ጤና የMHPAP አላማዎችን እና ግቦችን ለማሳካት የሂደቱን እድገት ይከታተላል።

**የዚህ ማጠቃለያ በቋንቋችሁ ለማግኘትና ስለመመሪያው እና የድርጊት መርሃ ግብሩ የበለጠ ለማወቅ የQR ኮድን ይቃኙ (ስካን ያድርጉ)**

**የኩዊንስላንድ ጤና የመድብለ ባህላዊ ማህበረሰቦችን ጤና እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ልዩ ልምዶቻቸውን እና አስተያየቶቻቸውን በማካፈል ለዚህ ፖሊሲ አስተዋፅዖ ያደረጉትን ሁሉ እናመሰግናለን።**

Queensland Government





| ቅድሚያ የሚሰጣቸው መስኮች | ዓላማዎች | እኛ የሰማነው |
|---|---|---|
| ቅድሚያ 1<br>**ቅድመ ጣልቃ ገብነት እና ቀድሞ መከላከል** | • ጥሩ የጤና እና የኑሮ ደህንነት ውጤቶችን ለማግኘት እና ለማስፈጸም የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች በተሻለ ለመረዳት ከመድብለ ባህላዊ ታሪክ/ዝርያ ካላቸው ሰዎች ጋር እንገናኛለን።<br>• እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያግዙ የጤና አገልግሎቶችን ለመንደፍ ከመድብለ ባህላዊ ማህበረሰቦች ጋር እንሰራለን።<br>• ከመድብለ ባህላዊ ታሪክ/ዝርያ የመጡ ሰዎች የራሳቸውን ጤና እንዲቆጣጠሩ፣ ከበሽታ እንዲርቁ እና የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ እንረዳለን። | **“የመከላከያ ውጥኖች በብቁ የጤና ባለሙያዎች የተደገፉ፣ ግን ደግሞ በኛ፣ በማህረሰቡ የሚመሩ፣ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ የህብረተሰቡን የመከላከል አቅም መገንባት።”** |
| ቅድሚያ 2<br>**ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የቋንቋ አገልግሎቶች እና የመገናኛ መሳርያዎች** | • የኩዊንስላንድ የጤና ሰራተኞች እንዴት፣ መቼ እና ለምን አስተርጓሚዎችን ማሳተፍ እንዳለባቸው እንዲያውቁ እናደርጋለን።<br>• በቋንቋ የተለያዩ ታሪክ ካላቸው ህብረተሰቦች የመጡ ሰዎች በመረጡት ቋንቋ መረጃ እንሰጣለን።<br>• የቋንቋ አገልግሎት የሚሰጠውን የሰው ኃይልን መደገፍን ጨምሮ፣ ለታካሚዎች የሚሰጠውን የቋንቋ አገልግሎት ጥራት እንቆጣጠራለን። | **“የቋንቋ መሰናክሎች ለህብረተሰባችን የጤና እንክብካቤ ትልቁ እንቅፋት ሆነው ቀጥለዋል።በጤናው ስርዓት ውስጥ ያሉትን የትርጉም አገልግሎቶች አጠቃቀም በደንብ ያልተረዳን እና ጥቅም ላይ ያልዋለ ነው።”** |
| ቅድሚያ 3<br>**ዘላቂ፣ ተደራሽ፣ ስለ የስሜት ቀውስ በቂ መረጃ ያለው እና ባህላዊ ደህንነቱ የተጠበቀ የጤና አገልግሎቶች** | • በኩዊንስላንድ የጤና አገልግሎት ታካሚዎችን የሚያከብር እና ከዘረኝነት እና አድሎ የጸዳ ባህል እንገነባለን።<br>• በቦርዶች እና በኮሚቴዎች ውስጥ የሚሳተፉት ከመድብለ ባህላዊ ታሪክ የመጡ ሰዎችን  ቁጥር እንጨምራለን ።<br>• የመድብለ ባህላዊ ማህበረሰቦች የጤና አገልግሎቶችን በሚያገኙበት ጊዜ መብቶቻቸውን እንዲረዱ እና እንዲጠቀሙበት እንደግፋለን።<br>• ታካሚዎች የጤና አጠባበቅ ስርዓቱን እንዲፈትሹ እና ደህንነት እንዲሰማቸው ለማድረግ ከባህል ጋር ተስማሚ የሆኑ ፕሮግራሞችን እናዘጋጃለን። | **“የማህበረሰቦቻችንን ፍላጎቶች በተሻለ መልኩ ለማሟላት የተለመደውን ልምምድ እንደየአስፈላጊነቱ ማሻሻል መቻል ቁልፍ ነው፣ ለምሳሌ ውስብስብ አሰራሩን በማሰስ ረገድ አጋዥ የሆኑትን መድብለ ባህላዊ ነርሶች።”** |
| ቅድሚያ 4<br>**ምርታማ አጋርነት፣ ትብብር እና ትስስር** | • ከመድብለ ባህላዊ ማህበረሰቦች ጋር ጠንካራ እና የተከበረ ግንኙነት እንገነባለን።<br>• የመድብለ ባህላዊ ማህበረሰቦችን ቀላል የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ከሌሎች የጤና ስርዓቱ አካላት ጋር እንሰራለን።<br>• የመድብለ ባህላዊ ማህበረሰቦች በተቻለ መጠን የተሻለውን ጤና እና ደህንነትን እንዲያገኙ ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር እንሰራለን። | **“ጤናን የሚወስኑ ማህበራዊ ጉዳዮችን ለመፍታት፣ ከማህበረሰብ እና ከሌሎች ዘርፎች ጋር በአጋርነት፣ በሁሉም የጤና ዘርፎች በትብብር የመስራት ኣስፈላጊነት የሚያሳዩ ብዙ ትምህርቶች ከ COVID-19 አሉ።”** |
| ቅድሚያ 5<br>**ብዝሀናት ያለው፣ አካታች እና በባህል ብቃት ያለው የጤና ሰራተኛ** | • የተለያየ የጤና ሠራተኛ ለመገንባት አካታች የሆኑ የምልመላ ኣሰራሮችን እንተገብራለን።<br>• ለኩዊንስላንድ የጤና ሰራተኞች ባህላዊ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምላሽ ሰጪ እንክብካቤን ለማቅረብ ተገቢውን ስልጠና እንሰጣለን።<br>• ከመድብለ ባህላዊ ታሪክ የመጡ የኩዊንስላንድ ጤና ጥበቃ ሰራተኞች  በስራ ቦታቸው ክብር ያላቸው፣ የተከበሩ እና ስልጣን እንዲሰማቸው እናደርጋለን። | **“የባህላዊ እና ሙያዊ ብዝሃነት በስርአቱ ውስጥ መንጸባረቁን የማረጋገጥ ኣስፈላጊነት ኣለ። ይህ ካልሆነ፣ ከማህበረሰቦቻችን አንዳንዶቹ በጤና የስራ ሀይል ውስጥ ላይወከሉ ይችላሉ። በመረጃው ውስጥ እኩል የሆነ የሰው ሃይል ብዝሃነት ስርጭት ያለው እና ከማህበረሰባችን ካሉ ሰዎች ጋር አብሮ ለመስራት ግንዛቤ እንዲኖረው የሰለጠነ የሰው ሃይል ማየት አለብን።”** |
| ቅድሚያ 6<br>**መድብለ ባህላዊ መረጃ እና ምርምር** | • የጤና አገልግሎትን ለማሻሻል ስለመድብለ ባህላዊ ማህበረሰቦች መረጃ የምንሰበስብበትን እና የምንተነትንበትን መንገድ እናሻሽላለን።<br>• የመድብለ ባህላዊ ማህበረሰቦችን በሚመለከቱ የጤና ጉዳዮች ላይ የበለጠ ምርምር እናደርጋለን።<br>• የመድብለ ባህላዊ ማህበረሰቦችን የጤና ፍላጎቶቻቸውን እና ውጤቶቻቸውን የበለጠ ለመረዳት በምርምር እናሳተፋለን። | **“ለህብረተሰባችን ባህላዊ ተገቢነት ያላቸውና ውጤታማ ኣገልግሎቶች ለማሻሻል የጥናት ማስረጃዎችን በማመንጨት እና ከማህበረሰቦቻችን ጋር በግምገማዎች እና በምርምር ለመስራት  መዋእለ ንዋይ አስፈላጊ ነው።”** |





SC2400222 /AMHARIC (አማርኛ)